# ጥናት አንድ ዘካርያስ 1፡1-2፡13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እዝራና ነህምያ ዘካርያስን የአዶ ልጅ በማለት መጥራታቸው በስህተት ወይም የቅራኔ ጉዳይ እንደሆነ አላምንም፤ ምክንያቱም፤ ልክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተለያዩ ሥፍራዎች እንደ አብርሃም ልጅ በሌሎች ጊዜያት ደግሞ የዳዊት ልጅ በመባል እንደሚጠራው ሁሉ፤ እነዚህ ሰዎችም የአዶ ልጅ ሲሉ የዘር ግንዱን ለመናገር እንጂ አዶ ወልዶታል ለማለት እንዳልሆነ ነው የማምነው። እግዚአብሄር ወደ ሕዝቡ እንዲመለስ ወይም ፊቱን እንዲመልስላቸው ካስፈለገ ሕዝቡ በቅድሚያ ማድረግ የሚገባቸው ነገር እንዳለ ነብዩ ግልጽ አድርጎ ያስታወቃቸው ሲሆን፤ እግዚአብሄር ወደ እነርሱ ለመመልስ፤ በቅድሚያ የእነርሱ ወደ እርሱ መመለስ አስፈላጊ እንደሆነ ነው የተነገራቸው።
2. የቀድሞ አባቶቻቸው ከክፉ ተግባራቸውና ሥራቸው እንዲመለሱ እግዚአብሄር የተለያዩ ነብያትን ቢልክላቸውም እንኳን ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት እነርሱን ከመስማት እንቢ እንዳሉ፤ በእግዚአብሄርም ላይ እንዳመጹ ሲናገር፤ እግዚአብሄር አምላክ ግን በነብያቱና በአገልጋዮቹ አማካኝነት ስለ አባቶቻቸው የተናገረው ነገር ሁሉ ተፈጻሚ እንደሆነ እናነባለን። ዘካርያስ ለህዝቡ ያስተላለፈው መልዕክት በሰሚዎቹ ዘንድ በአብዛኛው ተቀባይነትን እንዳገኘ ነው የማየው፤ ምክንያቱም፤ በቁ6 መጨረሻ ላይ ስናነብ "እነርሱም ንስሃ ገብተው እንዲህ አሉ…" በማለት ሕዝቡ የሰጠው ምላሽ ምን ዓይነት እንደነበረ ያሳየናል።
3. በቁ12-13 ውስይ "የእግዚአብሄር መልዓክ" በመባል ሲጠራ የምንመለከተው ስለ ኢየሩሳሌምና ይሁዳን አስመልክቶ የነበረውን ጥያቄ ለእግዚአብሄር ጸባዖት ሲያቀርብ፤ ለጥያቄው ምላሽ ምን መልስ እንደተሰጠው ከመናገሩ አስቀድሞ፤ ምላሹ በምን ዓይነት መንፈስ እንደተሰጠ ሲናገር፤ ደስ በሚያሰኝና በሚያጽናና ቃል እንደተመለሰለት እናነባለን። መልሱ የተሰጠበት መንፈስ ብቻ ሳይሆን የተመለሰለትም መልስ የሚያነቃቃ ሲሆን፤ ብዙ ተስፋዎችን የሰጠ ሲሆን፤ በአጭሩ ግን እግዚአብሄር ለኢየሩሳሌም በመቅናት በምህረት ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚመለስ፣ በጠላቶቻቸው ላይ እንደሚቆጣ፣ ብልጥግና እንደሚትረፈረፍና ሌሎችም ብዙ በረከቶች እየመጡላቸው እንደሆነ ተስፋ ይገባላቸዋል።
4. በእነዚህ ቁጥሮች በተለይም በቁ18-20 ውስጥ ዘካርያስ የተመለከተው ነገር አራት ቀንዶችን ሲሆን፤ ከእርሱ ጋራ ሲነጋገር ለነበረውም መልዓክ ያቀረበለት ጥያቄ "እነዚህ ምንድናቸው?" በማለት የተመለከታቸውን ቀንዶች ምንነት ለመረዳት የቀረበ ጥያቄ ነበረ። መልዓኩ ለነብዩ ዘካርያስ የመለሰለት መልስ፤ እነዚህ ያያቸው አራቱ ቀንዶች ይሁዳን፣ እስራኤልንና፣ ኢየሩሳሌምን የበታተኑ ቀንዶች እንደሆኑ ነው የሚያስረዳው።
5. ዘካርያስ ቀና ሲል የተመለከተው ነገር፤ በእጁ የመለኪያ ገመድ የያዘ ሰው ሲሆን፤ በዚህን ጊዜ ገመድ ምን እንደሆነ ስለሚያውቅ የጠየቀው ጥያቄ ከዚያ የተለየ ነበረ፤ ይኸውም "የት ልትሄድ ነው?" የሚል ጥያቄ ነው ያቀረበለት። ነብዩ በፊቱ ያየው የነበረውን ሰው ለጠየቀው ጥያቄው የሰጠው መልስ "የኢየሩሳሌም ርዝመትና፣ ስፋት ምን ያህል እንደሆነ ለመለካት መሄዴ ነው አለኝ" በማለት ያገኘው መልስ ምን እንደነበረ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦልናል።
6. ይህ መልዓክ ለዘካርያስ እንዲደርስ ለሌላኛው መልዓክ ከተናገረው ሃሳብ ውስጥ ስመለከት፤ በእኔ አመለካከት መልዓክት ፈጣኖች እንደሆኑ እየታወቀ በተጨማሪ ግን  እንዲሮጥና መልዕክቱን ለማስተላለፍ የበለጠ ፍጥነት እንዲጨምር  መጠየቁ ስለ መልዕክቱ አስቸኳይነት ነው የሚያስረዳኝ። ኢየሩሳሌም ቅጥር እንደሌላት ከተማ ትሆናለች ማለቱ ለጠላት የተጋለጠች ትሆናለች ለማለት ሳይሆን፣ እንዲያውም ቅጥሯ የእሳት ቅጥር የሆነው እግዚአብሄር ራሱ መሆኑን ሲጠቁመን ነው።
7. ለጽዮን የእልልታና የደስታ ምክንያት እንደሚሆን የተነገረው ነገር፤ የእግዚአብሄር ወደ እርሷ መምጣትና፤ በእርሷ መሃል ለመኖር መወሰኑ ነው። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር አምላክ ለኢየሩሳሌም ስላለው ጥንቃቄ የገለጸባቸውን ነገሮች አውጥተን መናገር የሚቻል ቢሆንም እንኳን፤ በእኔ አመለካከት ግን ዋነኛ ብዬ የማስበው በቁ8 መጨረሻ ላይ የሰፈረው "የሚነካችሁ የዓይኔን ብሌን እንደሚነካ ነው" የሚለው አነጋገር ነው።
8. እግዚአብሄር አምላክ ልጆቹ በጠላታቸው ፊት አንገታቸውን ደፍተው እንዲኖሩና ተስፋ በመቁረጥ አምላክ እንደሌለው ሕዝብ እንዲመላለሱ ሳይሆን፤ በጠላታቸው ላይ አንገታቸውን ቀና በማድረግ የድል ሕይወትን እንዲኖሩ ስለሚወድ የከበደባቸውን ቀንበር በመስበርና፣ እንዲሁም ጠላታቸውን የሚያስደነግጥላቸው እርሱ ብቻ እንደሆነ እንዲረዱ ነው እነዚህን አራቱን የእጅ ባለሞያዎች ለዘካርያስ ማሳየት የፈለገው፤ ስለዚህም እኛም ብንሆን ዓንገታችንን መድፋታችንና ተስፋ እንደሌለን ሆነን መመላለሳችን የእግዚአብሄር ፈቃድ እንዳልሆነ ልንረዳ ያስፈልገናል።

## <u>ጥናት ሁለት ዘካርያስ 3፡1-4፡14 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሚታዩት ተዋናኞች ዝርዝር እንደሚከተለው ይሆናል። በመጀመሪያ ደረጃ ስሙ የተጠቀሰው ሊቀ ካህኑ ኢያሱ ሲሆን፣ ቀጥሎ ደግሞ የእግዚአብሄር መልዓክ ተጠቅሷል፣ በሶስተኛ ደረጃ የሰፈረው ደግሞ ሰይጣን ሲሆን፣ በመጨረሻም የምንመለከተው እግዚአብሄርን ራሱን እናገኘዋለን። እነዚህ ሁሉ በተለያዩ ምክንያቶች ስማቸው የሰፈረ ሲሆን፤ በተለይ ግን የሰይጣን ሚና በዚህ ክፍል ውስጥ ኢያሱን በመክሰስ ላይ እንደነበረ ነው የምናነበው። ሰይጣን በዚህ ክፍል ውስጥ ኢያሱ ላይ ብቻ ያተኮረ ይሁን እንጂ ራዕ 12፡10 ላይ ዮሐንስ ከሚሰጠው ስም የምንረዳው የኢያሱ ከሳሽ ብቻ ሳይሆን የወንድሞቻችን ሁሉ ከሳሽ እንደሆነ አረጋግጧል።
2. ሰይጣን የወንድሞቻችን ሁሉ ከሳሽ እንደሆነ ሌሎችን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንኳን ባንጠቀም በዚሁ ክፍል ለማረጋገጥ የሚቻል የሚመስለኝ፤ ይህ ኢያሱ የተባለ ሰው ሊቀ ካህን እንደሆነ የተነገረን በመሆኑና በዚህ ሃላፊነቱ የእስራኤልን ሕዝብ ሁሉ የሚወክል ስለሆነ ይህ ክስ በእርሱ ላይ ብቻ ያነጣጠረ ይምሰል እንጂ ህዝቡን ሁሉ የሚከስ እንደሆነ ነው የማየው።
3. ጠላቱ ሰይጣን ሊቀ ካህኑን ሊከስበት የሚችልበት ተጨባጭ መረጃ እንደነበረው በግልጽ ማየት የሚያስችለን በቁ3 እና ቁ4 ላይ የሰፈረው ሃሳብ ነው፤ ይኸውም ኢያሱ የለበሰው ልብስ እድፋም እንደነበረ ይህም እድፋም ልብስ ትርጉሙ ሃጥያት እንደሆነ በእነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ የምናይ ሲሆን፤ ሰይጣን ለመክሰስ በቂ መረጃ እንደነበረው ነው የምናየው። የሰይጣን ክስ በኢያሱ ሐጥያት ላይ ያተኮረ እንደሆነ ሲታወቅ፤ እግዚአብሄር ለባርያው የሰጠው መፍትሔ ግን ሃጥያቱን ከማስወገድ ባሻገር እንደሆነ ይታያል፤ ይኸውም አሮጌውን ልብሱን ማውለቅ ብቻ በቂ ሆኖ ስላላገኘው አዲስ ልብስ ማለትም ከራሱ የሆነ ጽድቅንም እንዳለበሰው ነው የምናየው።
4. ጠላቱ ይከሰው ከነበረበትና ኢያሱ ከነበረበት የሐጥያት አዘቅት ውስጥ እግዚአብሄር በምህረቱ ሃጥያቱን አስወግዶ የራሱን ጽድቅ ማልበሱ ኢያሱን ከሃላፊነት ነጻ የሚያደርገው እንዳልሆነ እነዚህ ቁጥሮች የሚያሳዩን ሲሆን፤ በማስጠንቀቂያ መልክ ለኢያሱ የተነገረው ሃላፊነት "በመንገዴ ብትሄድ፤ ትዕዛዜንም ብትጠብቅ" በማለት ወደፊት የሚጠበቅበትን ሃላፊነት ይነግረዋል። በእነዚህ እግዚአብሄር በሰጠው መንገዶች ቢራመድ፤ ቤቱን እንደሚያስተዳድር፣ በአደባባዮቹ ላይ ሃላፊ እንደሚሆንና፣ በዚያ በቆሙት መሃልም ቦታ እንደሚሰጠው ነው የተገባለት ተስፋ።
5. እግዚአብሄር ለኢያሱ እየነገረው ያለው መልዕክት በእርሱ ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር ከመፈለጉ የተነሳ ከኢያሱ ጋራ በአገልግሎት የተሰማሩትና አገልግሎቱ ላይ ተሳትፎ ያላቸው ሰዎች ሁሉ እንዲሰሙት ያዘዋል፤ ምክንያቱንም ሲነግረው እነዚህ ሰዎች ወደፊት ለሚመጡት ሰዎች ሁሉ እንደወኪል ሆነው ሊያገለግሉ ስለሚችሉ ነው ይለዋል። መልዕክቱን ኢያሱ፣ ከእርሱ ጋራ የሚያገለግሉት ሰዎችና፣ ሌሎቹም እነርሱ ሊወክሏቸው ያሉት ሰዎች ሁሉ እንዲያውቁት አንገብጋቢ ሆኖ የተገኘበት ምክንያት ሊመጣ ያለውን መሲሁንና ጥላ ከሆነው ሊቀ ክህነት በተሻለ እውነተኛው ሊቀ ካህን ስለ ሆነው ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ የሚጠቁም ስለሆነ ነው።
6. ዘካርያስ በተለያዩ ጊዜያት መልዓኩ እንዲያይ ላደረገው የተለያዩ ራዕዮች ይኸኛውንም ጨምሮ ማለት ነው፤ ሲያደርግ የምናገኘው አንዱና ዋነኛው ነገር ያያቸው ነገሮች ምን ማለት እንደሆኑና ወይም ደግሞ ሌላ ያልገባውን ነገር በማንሳት ለመልዓኩ ጥያቄን ማቅረቡ ለሁሉ ማዕከላዊ ነገር ነው ብዬ ነው የማምነው። ከመጀመሪያው ራዕይ አንስተን ስንመለከት ዘካርያስ ጥያቄ የሆነበትን ነገር ሲጠይቅ መልዓኩ የፍርድ ነገር ሳይናገርና አለማወቁን ሳያጣጥል ተገቢውን መልስ ሲሰጠው ነው የምናየው።
7. በቁ6-9 ውስጥ እግዚአብሄር ለዘሩባቤል ሊያስተላልፍ የፈለገው ዋነኛ መልዕክት ነው ብዬ የማምነው፤ በመጀመሪያ ደረጃ መረዳት የሚኖርበት ሥራውን የሚሰራው እግዚአብሄር ራሱ እንጂ ዘሩባቤል እንዳልሆነ በመንገር ሸክሙን ከእርሱ በማንሳት በእግዚአብሄር ላይ ያስቀምጣል፤ በተጨማሪም ደግሞ ትልቅ መስሎ በፊቱ የቆመው ጠላቱም እግዚአብሄር በባሪያው ፊት እንደሚደለድልለት በመንገር ያነቃቃዋል። የሕዝቡ ለወደቀበትና የተስፋ ጭላንጭል ለጠፋበት መሪ በተለይም ከእግዚአብሄር ከራሱ የዚህን ዓይነት የማበረታቻ ቃል መስማት ማለት ለመሪ ትልቅ መነቃቂያና ተስፋ እንደሚሆንለት ጥርጥር የለውም።
8. በእኔ አመለካከት በተለይም በሐጌ ትንቢት ውስጥ በሐጌ 1፡1፣ 12፣ 14፣ 2፡2፣ 4 ውስጥ ስማቸውን በአንድነት ሰፍረው የምናያቸውና በዚህ በዘካርስም ውስጥ በተናጠል ይሁን እንጂ በምዕ3 እና በምዕ4 ውስጥ የምናያቸውን የእግዚአብሄር አገልጋዮች ሆነው የተነገሩንን ኢያሱንና ዘሩባቤልን የሚናገር እንደሆነ ነው የማምነው።
9. በዚህ ክፍል ውስጥ ተከሳሹ ኢያሱ ይሁን እንጂ ለክሱ ምላሹን ሲሰጥ የምንመለከተው ራሱ እግዚአብሄር እንደሆነ ነው፤ ስለዚህም የወንድሞቻችን ከሳሽ በመባል የታወቀው ሰይጣን ጊዜው ደርሶ እስከሚጣልበት ጊዜ ድረስ እኛንና ወንድሞቻችንን ሁሉ መክሰሱን እንደማያቆም፤ ሆኖም ግን በአብ ዘንድ ጠበቃ ስላለልን ስለ እኛ የሚከራከርልን ጠበቃችን መሆኑን አንዘነጋም።

## ጥናት ሶስት ዘካርያስ 6፡9-7፡14 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በእነዚህ ሶስት ቁጥሮች ውስጥ ዘካርያስ እንዲያደርገው በእግዚአብሄር የታዘዘው ነገር፤ ከባቢሎን ከተመለሱት ምርኮኞች በተለይም ሶስቱን በስም በመጥቀስ ወርቅና ብር ወስዶ በዚያኑ ቀን ደግሞ ወደ ሶፎንያስ ልጅ ወደ ኢዮስያስ ቤት በመውሰድ አክሊል አድርጎ እንዲሰራው፤ ከዚያም የሰራውን አክሊል በሊቀ ካህኑ በኢያሱ ራስ ላይ እንዲያኖረው ነው የተነገረው። ይህንን በዘካ 6፡11 ላይ እግዚአብሄር ያዘዘውን ትዕዛዝ ልዩ የሚያደርገው ነገር ቢኖር፤ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ንጉሥና ክህነት የአንድ ሰው ሃላፊነት ተደርጎ አያውቅም፤ ስለዚህም ነው በ2ኛ ዜና 26 ውስጥ ንጉሱ ዖዝያን እጣን እንዳያጥን በካህናቱ የተከለከለውና፤ በተጨማሪም ከእግዚአብሄር ዘንድ ለምጽ ያገኘው። በዚህ ክፍል ግን ኢያሱ ሊቀ ካህን ሆኖ እያለ የንጉሥነትንም አክሊል እንዲደፋለት መታዘዙ የተለየ ያደርገዋል።
2. እነዚህ በዘካ 3፡8፣ በኢሳ 4፡2፣ 11፡1፣ ኤር 23፡5፣ 33፡15 እና የመሳለሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አብዛኛዎቹ ግልጽ በሆነ መንገድ መሲሁን የሚጠቁሙ በመሆናቸውና በተለይም ደግሞ በዘካ 3፡8 ላይ የሰፈረው ሃሳብ እንደነዚሁ ክፍሎች በመሲሁ ላይ ያተኮረ በመሆኑ፤ በዚህ ሥፍራ “ቅርንጫፍ” በማለት የተናገረው ስለ መሲሁ እንደሆነ ነው የማምነው።
3. በእኔ አመለካከት በቁ12 ላይ “ቅርንጫፍ” በመባል የተጠራውና ከተለያዩ ክፍሎችም በመመልከት መሲሁ እንደሆነ ያልነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ የሚሰራውም ቤተ መቅደስ ዘሩባቤል እየሰራ እንዳለው ዓይነት ሳይሆን መንፈሳዊ ቤተ መቅደስ ልክ በኤፌ 2፡19-22 እና በ1ኛ ጴጥ 2፡5 ላይ የምናነበውን ዓይነት ቤተ መቅደስ የሚናገር እንደሆነ ነው የማምነው። በዘካ 6፡13 ውስጥ የምናየው ሃሳብ መሲሁ ንግሥናውንና ክህነቱን በአንድነት በሚይዝበት ወቅት፤ በንጉሥና በካህን መሃል ሊከሰት የሚችለው ዓይነት ቅራኔ ሊኖር እንደማይችል ሲነግረን፤ 2ኛ ዜና 26 ላይ ያለው ግን የሚያኃላልን ሃሳብ በንጉሥና በካህን መሃል ሊከሰት የሚችለውን ችግር መሆኑ ሃሳቡን ግልጽ ያደርግልናል።
4. ይህ በዘካርያስ ምዕራፍ 6 ውስጥ የምናነበው አክሊሉንና በራሱ ላይ እንዲደረግለት የታዘዘውን ሊቀ ካህን ሰው ኢያሱን በዚህ ክፍል ውስጥ እንዲሰፍር ሲያደርግ ወደፊት ሊመጣ ላለው ካህንና ንጉሥ ማለትም ለመሲሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ በመታሰቢያነት እንዲያገለግል እንጂ እውነትም ኢያሱ በኢየሩሳሌም ላይ ንጉሥ ሆኖ ያስተዳድራል የሚለውን ሃሳብ ለመግለጽ እንዳልሆነ በተለይም ቁ14 ላይ በጊዜው በክህነት አገልግሎት ላይ ተሰማርተው የሚገኙትን ሰዎች ስም በመዘርዘር ይናገራል።
5. ***እነዚህ የቤቴል ሰዎች በባቢሎን እየኖሩ ሳሉ በመለማመድ ላይ ያሉትን የሐዘንና የመጾምን ልምምድ አሁንም መቀጠል ይኑርባቸው ወይም አይኑርባቸው የሚለውን ነገር ስላልገባቸው ለዚህ ጥያቄአቸው መልስ ለማግኘት እንደ አንድ ሰው በመሆን ከመካከላቸው ሰዎችን መርጠው እግዚአብሄርን ለመጠየቅ እንደላኩ ነው የምናየው። እግዚአብሄር ለጥያቄአቸው የሰጣቸው ምላሽ ከበድ ያለና የጠበቁት ባይሆንም እንኳን፤ እነዚህ የቤቴል ሰዎች ለጥያቄአቸው መልስን ለማግኘት ወደ ሰው ሳይሆን ወደ ምንጩ ወደ እግዚአብሄር ጥያቄአቸውን ይዘው መምጣታቸው በራሱ በእኔ አመለካከት ትልቅ ነገር እንደሆነ እመለከታለሁ።
6. በዚህ ቦታ እግዚአብሄር ጥያቄአቸውን በጥያቄ ሲመልስ የተናገረው ነገር ቢኖር፤ የጾሙትና ያዘኑት እውነት ለእርሱ እንዳልሆነ፤ ከዚህም ባሻገር ይበሉና ይጠጡ የነበረውም ለራሳቸው እንጂ ለእርሱ እንዳልነበረ ነው የተናገረው። በእኔ አመለካከት ይህ ክፍል በእስራኤል ህይወት በተግባር የታየውን የሚገልጽ ሲሆን፤ በሮሜ 14፡6 ውስጥ ጳውሎስ የሚናገረው ደግሞ በመመሪያ መሰረት ይህንኑ ሃሳብ አስፍሮልን ነው የምናገኘው። እግዚአብሄር ቀድሞም በነብያት በኩል ለአባቶቻቸው ተናገርኩ የሚለው ልክ በኢሳ 58፡6-7፣ በኤር 22፡3 እና በመሳሰሉት ትንቢቶች በተለያዩ ነብያቱ አማካኝነት የነገራቸውን ሃሳብ ነው።
7. ምንም እንኳን እግዚአብሄር ለእነዚህ ሰዎች ቀጥተኛ በሆነና በማያሻማ መንገድ እንዲመለክ የሚፈልግበትን መንገድ ቢናገራቸውም እንኳን፤ ከቁ11 እና ቁ12 እንደምንመለከተው ምላሻቸው የእንቢተኛነትና እነርሱ በመሰላቸው መንገድ አምልኳቸውን ማካሄድ እንደቀጠሉ ነው የምናነበው፤ ስለሆነም እግዚአብሄር በዚህ አስተሳሰባቸውና ድርጊታቸው እጅግ እንደተቆጣ ከቁ12 ማየት እንችላለን።
8. ከቁ8 ጀምሮ ቅደም ተከተል ባለው መንገድ እነዚህ ሰዎች ትክክለኛው እግዚአብሄር የሚወደው አምልኮ ምን እንደሆነ ተነግሯቸው፤ እነርሱም ይህንን የእግዚአብሄርን ፈቃድ ምን እንደሆነ ተረድተው ነገር ግን በራሳቸው መንገድ መሄድን በመምረጣቸው፤ ይህንን እንቢታቸውን እግዚአብሄር በዝምታ ለማለፍ አልፈለገም፤ ስለዚህም በቁ13-14 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ እንዳመጣባቸው እናያለን፤ ይህም ማለት ሲጠሩት እንደማይሰማቸው፣ በአህዛብ መሃል በተናቸው፣ ምድራቸውን ደግሞ ባድማ አደረጋት።

# ጥናት አራት ዘካርያስ 8፡1-23 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እንድትወድቅና እንድትደመሰስ ለፈቀዳት ለጽዮን ከተማ ዛሬ እግዚአብሔር መልሶ ቀንቻለሁ በማለት ስለተናገረበት ሁኔታ ሁለት ምክንያቶችን አያለሁ፤ ከእነዚህም አንደኛው አሁን ቅሬታዎቹ የእግዚአብሄርን ቤት ለመሥራት ኑሯቸውን ሁሉ ትተው ለመምጣት የወሰኑና ለእግዚአብሄር ነገር ሥፍራ የሚሰጡ ሰዎች በመገኘታቸውና፤ በተጨማሪ ደግሞ ቀደም ብለን ያየናቸው በባቢሎን እየኖሩ ያሉ የቤቴልን ሰዎች የመሰሉ ነገራቸውን ከእግዚአብሄር ጋራ ለማስተካከል የሚሞክሩ ዓይነት ሰዎች መገኘታቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ እግዚአብሄር የወሰነው የሰባ ዓመቱ ጊዜ መድረሱ እንደሆን ነው ለእኔ የሚገባኝ።
2. የእግዚአብሄር ወደ ጽዮን መመለስና በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ የማደሩ ውጤት ከሆኑት ነገሮች መሃል በቁ4-5 ውስጥ የማያቸው ሁለቱ፤ የመጀመሪያው የሽማግሌዎችና የአሮጊቶች አደባባዩን መሙላትና ከእነምርኩዛቸው የመታየት ነገር ሲሆን፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሴቶች ማህጸን ተከፍቶ ብዙ ሴቶችና ወንዶች ሕጻናት አደባባዮችን መሙላታቸው ነው። በተለይ የመጀመሪያው ማለትም ብዙዎችን በእርጅና ማየት በረከት የሚሆንበት ምክንያት፤ እድሜ ሳይጠገብ በአጭር መቀጨት ማክተሙ፣ እግዚአብሄር ደግሞ ሕዝቡን በረጅም እድሜ መባረኩና የእድሜ ባለጠግነት ለብዙዎች እንዲለማመዱ በምርኩዝ መሄድ እስኪችሉ ድረስ መቆየት እንዲችሉ ማድረጉ የበረከቱ ምልክት ነው።
3. አስቀድመን እንዳልነው የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሄርን በረከት ከተለማመደና የዚህ ዓይነቱን ሁኔታ ማየት ካቆመ ምናልባትም ዘመናት ያለፉ ሊሆን ይችላል፤ ስለዚህም አብዛኞቹ በባቢሎን የተወለዱና የቀደመውን ነገር ስለማያውቁ ይህ ዛሬ እግዚአብሄር ሊያደርግ ያለው ነገር በሕይወት ዘመናቸው ተለማምደውት የማያውቁት የበረከት አይነት ስለሆን የመደነቃቸው ምክንያት ያ ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ። በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ ሊፈጸም ላለው በጎ ነገር ሁሉ ምንጩ እግዚአብሄር ራሱ እንደሆነ ነው የሚጠቁመን።
4. በዚያን ሰዓት በዘካሪያስ ውስጥ ለህዝቡ እየተናገረ ያለውን የማበረታቻ መልዕክት እግዚአብሄር እያነጻጸረ ያለው፤ ሕዝቡ ገና ከባቢሎን ተመልሶ የቤተ መቅደሱ መሰረት ሲጣል ሕዝቡን ለማበረታታት ይነገር ከነበረው የትንቢት መልዕክት ጋራ ነው። “ከዚያ በፊት…” በማለት በቁ10 ላይ ከባቢሎን የተመለሰው ቅሬታው ሕዝብ የእግዚአብሄርን ቤተ መቅደስ መሰረት ለመጣል እስከመጣበት ጊዜ ድረስ በዚያ ይኖሩ የነበሩት ሕዝቦች ሰርተው ደመወዝ ሊያገኙ የሚችሉበት ሥራ አልነበራቸውም፤ ሰዎች አንደኛው በሌላው ላይ የሚነሳበት ሁኔታ ስለነበረ ከቤታቸው ወጥተው ለመግባት እንኳን ሁኔታው አስተማማኝ አልነበረም።
5. ለሕዝቡ እግዚአብሄር በቁ 12-13 ውስጥ ሲገባላቸው የምንመለከታቸው የበረከት ቃል ኪዳኖች፤ የዘሩት ዘር ጥሩ ሆኖ እንደሚበቅል፣ ወይናቸው ፍሬ እንደሚያፈራ፣ ምድሪቱ አዝመራዋን በጊዜው እንደምትሰጥ፣ ሰማያት ጠላቸውን እንደሚሰጡ፣ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለቅሬታዎቹ ርስት አድርጎ እንደሚሰጥና በመጨረሻም የእርግማን ምሳሌነታቸውን አስቀርቶ የበረከት ምሳሌ ያደርጋቸዋል። ይህንን ሁሉ በረከት እንደሚሰጣቸው ከተናገረ በኋላ፤ በዚህ ሁሉ ከእነርሱ የሚጠብቀው አንድ ነገር ቢኖር፤ እንዳይፈሩና፣ ቤተ መቅደሱን ለመስራት እጃቸውን እንዲያበረቱ ነው።
6. እግዚአብሄር አምላክ የወደደውን ለማድረግ ከልካይ እንደሌለው የሚያሳየን ክፍል በቁ14 እና በቁ15 ውስጥ፤ “ጥፋት ላመጣባችሁ እንደወሰንኩ”፣ “መልካም ነገርን ላደርግ ወስኛለሁ” የሚሉት አነጋገሮች፤ ክፉንም ሆነ መልካምን ለማድረግ ውሳኔውን የሚከለክለው እንደሌለ ያሳየኛል። እግዚአብሄር እንደሚጸየፋቸው የተናገራቸውና ከእነርሱ እንደሚጠብቅባቸው ያስታወቃቸው አራቱ ነገሮች፤ እርስ በእርሳቸው እውነትን መነጋገር፣ በአደባባዮቻቸው እውነትንና ትክክለኛ ፍርድን እንዲያሰፍኑ፣ በባልንጀሮቻቸው ላይ ክፋትን እንዳያውጠነጥኑና፣ በመጨረሻም በሐሰት መማልን እንዳይወዱ የሚሉ ናቸው።
7. በቁ3 ላይ እግዚአብሄር በሕዝቡ በእስራኤል መሃል እንደገና መኖሪያውን እንደሚያደርግና በእርሱ በመካከላቸው መኖር የተነሳ ብዙ ዓይነት የበረከት በሮች እንደሚከፈቱላቸው ተመልክተናል፤ ሆኖም በዚህ በቁ20-23 ውስጥ የምንመለከተው ነገር የእግዚአብሄር ሕዝብ በረከትን ሲያገኝ ለራሱ ብቻ ሳይሆን አልፎ ለሌሎች በረከት እንዲሆን በመሆኑ፤ ይህ ክፍል በረከቱ ወደ አህዛብም የመዛመቱን ነገር የሚጠቁሙ ናቸው ብዬ አምናለሁ።
8. በቀደመው ምዕራፍ ማለትም በምዕራፍ 7 ውስጥ እንደተመለከትነው አባቶቻቸው እግዚአብሄርን ባለመታዘዛቸውና በነብያቱ የነገራቸውን ነገሮች ሁሉ እንቢ በማለታቸው ለምርኮ እንደተሰጡ፤ ምድሪቱ ደግሞ ባድማ ለመሆን እንደበቃች አይተናል። በዘካ 8፡3 ላይ ግን የምናየው ነገር የከተማይቱ ስም እንደሚቀየር፤ እንዲሁም የተራራውም ስም ሳይቀር የሚቀየርበት ጊዜ እንደደረሰ ነው ነብዩ ዘካሪያስ የሚናገረው፤ ይህም የሚሆንበትን ምክንያት ሲገልጽ እግዚአብሄር ወደ ጽዮን በመመለሱና በኢየሩሳሌም ውስጥ በማደሩ ምክንያት እንደሆነ ይነግረናል።